ቁ.1
(ሰኔ 2012)

ነፃነትና እኩልነት ፓርቲ

የነፃነት ወግ

በነፃነትና እኩልነት ፓርቲ የሚዘጋጅ የፓርቲው መጽሄት

ጥሞና

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ

ኢኮኖሚያዊ እና ስትራቴጂያዊ ፋይዳ

"ከታሪካዊ መብት ተፈጥሯዊ መብት ይቀድማል"

ቁ.1
(ሰኔ 2012)

የነፃነት ወግ

የነፃነትና እኩልነት ፓርቲ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና የትግል ስልቶች የሚተነተኑበት የንድፍ ሀሳብ እና አማራጭ የፖሊሲ ሀሳቦች የሚዳሰሱበት የፓርቲው ወርሃዊ መጽሔት ነው።

❋ ❋ ❋

አዘጋጅ፡ የነእፓ ህዝብ ግንኙነት
ስልክ፡ 011 381 0080
ፋክስ፡ 011 381 0065
ኢሜይል፡ fepeditorial@gmail.com
ድረገጽ፡ www.fepethiopia.com

02
ጥሞና

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ

07
የሃሳብ ሜዳ

ሰብአዊ መብትና የዴሞክራሲ ስርአት

09
ሃፀ ወግ



የህገ-መንግስት ትርጓሜ

04
ከመሰናበቻው



የኮቪድ 19 ወረርሽኝና ፌደራሊዝም

11
መዝታ ገፅታ

ጌሪማንደሪንግ
(Gerrymandering)

ጥሞና

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ

ኢኮኖሚያዊ እና ስትራቴጂያዊ ፋይዳ

"ከታሪካዊ መብት ተፈጥሯዊ መብት ይቀድማል"

ኢትዮጵያ ሰፊ እና ገና ጥቅም ላይ ያልዋሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ባለቤት ስትሆን፣ ወንዞቿ ትልቁን ድርሻ ይይዛሉ። ሃገራችን በቀጥር በርከት ያሉ ትንንሽ፣ መካከለኛ እና ትልልቅ ወንዞች ባለቤት መሆኗን ተከትሎ "የአፍሪካ የውሀ ማማ" የሚል ስም አሰሰጥቷታል። ዓባይ የዓለማችን ረዥሙ ወንዝ ሲሆን "የአፍሪካ ወንዞች አባት" በመባል ይሞካሻል። ስም እና ዝናው በአፍሪካ ብሎም በዓለም የገነነው የኛው አባይ 86% የውሀ ምንጩ ለሆነችው ኢትዮጵያ እና ህዝቦቿ ብዙም ሳያገለግል ብዙ ሺህ አመታት ካለፉ በኃላ ከዘጠኝ ዓመት በፊት በመጋቢት ወር ኢትዮጵያ ከወንዙ ፍትሀዊ እና ምክንያታዊ (equitable and reasonable) ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችላትን ውሳኔ በመወሰን ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ለመገደብ የመሰረት ድንጋይ ተጣለ።ኢትዮጵያ ይህንን መብቷን እና ፍላጎቷን እውን ሳታደርግ ብዙ ዘመናት ያለፉ ሲሆን ለዚህም ውስጣዊ እና ውጫዊ ተግዳሮቶች እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ። ግድቡን ለመገንባት ከፍተኛ የአቅም ውስንነት እና የፖለቲካ ቁርጠኝነት አለመኖር ፕሮጀክቱ ለብዙ ትውልድ በህሳብ ብቻ ተገድቦ እንዲቆይ አድርጎታል።

ኢትዮጵያ ከድህነት እና ኋላቀርነት ተላቅ ፈጣን እና ዘላቂ ኢኮኖሚ በመገንባት ህዝቦቿን ከረሀብ እና ከልመና ለማላቀቅ በምታደርገው ጥረት የተፈጠሮ ሀብቷን አሟጣ መጠቀም ግድ ይላታል። ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጀርባ ያለው መሰረታዊ ሀቅም ይኽው ነው። የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ለኢትዮጵያ እና ለሌሎች የተፋሰሱ ሀገራት ሰፊ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ጥቅሞችን እና እድሎችን እንደሚፈጥር ብዙዎች ይስማማሉ። 74 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሀ የመያዝ አቅም ያለው የህዳሴ ግድብ 6000 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል እንደሚያመነጭ የሚጠበቅ ሲሆን በማደግ ላይ ላለው የሀገራችን ኢኮኖሚ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

የግድቡ ግንባታ መጀመር ከታችኛው የተፋሰስ ሀገራት በተለይም ከግብጽ ጋር ከፍተኛ የዲፕሎማሲ እና የፖለቲካ ቀውስ አስነስቷል። አባይን ለብዙ ዘመናት በብቸኝነት ስትጠቀም የቆየችው ግብጽ ኢትዮጵያ ከወንዙ ፍትሀዊ ተጠቃሚ ለመሆን የጀመረችውን ጉዞ ከተቻለ ለማስቆም ያ ካልሆነ የግድቡን የግንባታ ሂደት ብሎም አጠቃቀም የሚቻለውን ያህል ዝቅ ለማድረግ በሙሉ አቅሟ በመንቀሳቀስ ላይ ትገኛለች። ውጥረት ተለይቶት የማያውቀው የአባይ ፖለቲካ በህዝብ ብዛት፣ በተፈጥሮ ሀብት መመናመን እና በውሀ እጥረት ምክንያት ይበልጥ እየተካረረ የመጣ ሲሆን የህዳሴው ግድብ መጀመር ውጥረቱን አባብሶታል።

በህዳሴ ግድብ ዙሪያ የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ ከግድቡ ግንባታ ማግስት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በተለያየ ደረጃ በርካታ ፖለቲካዊ እና የቴክኒክ ውይይቶች ተካሂደዋል። ኢትዮጵያ፣ ሱዳን እና ግብጽ በቀጥታ ከሚያደርጉት ግንኙነቶች በተጨማሪ በሶስተኛ ወገን አማካኝነት ውይይቶች የተካሄዱ ሲሆን ግብጾች "ታሪካዊ መብት" ብለው በሚጠሩት እና በአባይ ላይ ብቸኛ ተጠቃሚ እና የበላይ ተቆጣጣሪ የመሆን ኢ-ፍትሀዊ አቋም ምክንያት ከስምምነት ላይ መድረስ አልተቻለም። እ.አ.አ በ1929 እና በ1959 በቅኝ ግዛት ስር የተፈረሙ ውሎች ኢፍትሀዊ እና ህጋዊ መሰረት የሌላቸው እንደ ሆኑ ጠንቅቆ የሚያውቀው የግብጽ መንግስት የኢትዮጵያን የፍትሀዊ

ተጠቃሚነት ጥያቄ ተቀብሎ ውጤታማ ውይይት ለማድረግ አሻፈረኝ እንዳለ ዘጠኝ አመታት ፈጅቶበታል።

በአሜሪካ የገንዘብ ሚኒስቴር እና በዓለም ባንክ ታዛቢነት ሲካሄድ የቆየው ውይይት በግድቡ ዙሪያ ከሚደረጉ ድርድሮች አንዱ ሲሆን በታዛቢነት የተሳተፉት ሁለቱ አካላት የኢትዮጵያን ጥቅም በሚጻረር ግልጽ የሆነ አቋም በመያዛቸው ውይይቱ ያለ ውጤት ተጠናቋል - ኢትዮጵያም ራሷን ከውይይቱ አግልላለች። ኢትዮጵያ በወንዙ ላይ ያላትን ተፈጥሯዊ እና ህጋዊ መብት ለማስከበር በሚያስችሉ መድረኮች ላይ ተገኝታ አቋሟን ማሳየት ብሎም በግብጽ በኩል የሚሰራጩ መሰረተ ቢስ መረጃዎችን ለማክሸፍ መንቀሳቀሷ አስፈላጊ ሲሆን፣ መድረኮቹ አድሏዊ እና ግልጽ የፖለቲካ ወገንተኝነት ሲያራምዱ ድርድሩን ማቋረጥ ተገቢ ነው።

ዓለምአቀፍ የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ስምምነት እንደ አባይ ባሉ በርካታ ሀገራትን የሚያዋስኑ ወንዞች አጠቃቀም በተመለከተ መንግስታት የተፋሰሱን ሀገራት ፍትሀዊ ተጠቃሚነት በሚጎዳ እና ጉልህ ተጽእኖ በሚያሳድር ሁኔታ ተጠቃሚ መሆን እንደሌለባቸው ይደነግጋል። ከዚህ ዓለምአቀፍ ስምምነት በተጻራሪ ግብጽ ለብዙ ሺህ ዓመታት በዓባይ ላይ ብቸኛ ተጠቃሚ ሆና የቆየች ሲሆን ሌሎች ሀገሮች የድርሻቸውን እንዳይጠቀሙ በሙሉ ኃይሏ ስትከላከል ቆይታለች። የግድቡን ግንባታ በመቃወም ግንባር ቀደም ሚና በመጫወት ላይ ያለችው ግብጽ ግድቡ በውሀ አጠቃቀም የጎላ ጉዳት እንደማያደርስ ብቻም ሳይሆን ሌሎች በርካታ የጎንዮሽ ጥቅሞች እንዳሉት በሚገባ ታውቃለች። የህዳሴው ግድብ በክረምት በተለይ ሱዳን ውስጥ የሚከሰተውን የጎርፍ አደጋ ስለሚያስቀር ሱዳን ጎርፉ የሚያስከትለውን ከፍተኛ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ለመከላከል በየአመቱ የምታወጣውን ከፍተኛ ወጪ ያስቀራል። በተጨማሪም ሱዳን እና ግብጽ በአባይ ላይ የገነቧቸው ግድቦች በደለል እንዳይሞሉ የህዳሴው ግድብ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

> በድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ዉሀ አጠቃቀም ታሪክ የላይኛው ተፋሰስ ሀገራት የበላይነት እና የተሻለ ተጠቃሚነት አላቸው። የአባይ ጉዳይ የተገላቢጦሽ ነው።

የህዳሴው ግድብ እንደ ስሙ ለሀገራችን ህዳሴ ያለው ፋይዳ የትየለሌ ነው።ከግብርና ወደ ኢንደስትሪ በመሸጋገር ላይ ያለው የሀገራችን ኢኮኖሚ የተሳካ መዋቅራዊ ሽግግር ለማድረግ ወሳኙ ግብአት በቂ እና አስተማማኝ ኃይል ነው።አሁን ላይ ያሉንን የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ምርታማነታቸውን ለማሳደግ እና ሌሎች ዘመናዊ እና ግዙፍ ኢንደስትሪዎችን ለማቋቋም ከምንም በፊት አተስማማኝ እና በቂ የኃይል አቅርቦት የግድ ይላል። ከኢንደስትሪው ጎን ለጎን እጅግ ኋላቀር እና ባህላዊ በሆነ መንገድ ለብዙ ዘመናት የዘለቀውን የሀገራችንን የግብርና ዘርፍ በማዘመን የዘርፉን ምርታማነት ለማሳደግ የኃይል አቅርቦቱ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ሰፊ እና ለግብርና ምቹ የተፈጥሮ ኃብት ያላት ሀገራችን ከዘርፉ እያገኘችው ያለው ጥቅም ኢምንት ሲሆን ለዚህም አንዱ ምክንያት በቂ የኃይል አቅርቦት አለመኖር መሆኑን በዘርፉ የተካሄዱ ጥናቶች ያሳያሉ።

የአነስተኛና መካከለኛ ኢንደስትሪዎችን ለማስፋፋት እና በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሀገራችን ወጣቶች የስራ እድል ለመፍጠር ዋና ማነቆ የሆነው የኃይል አቅርቦት እጥረት ነው። በፍጥነት እያደገ ያለው የአገልግሎት ዘርፍ ቀጣይነቱ በኃይል አቅርቦት ላይ የተንጠለጠለ ነው። የሀገራችንን ገጽታ ለመቀየር፣ ቀጠናዊ እና ዓለምአቀፋዊ ተሰሚነታችን እና ተጽእኖ ከፍ ለማድረግ፣ በዓለም የውሀ ፖለቲካ (Hydro politics) ጉልህ ሚና እንዲኖረው የህዳሴው ግድብ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። የህዳሴው ግድብ እነዚህ እና ሌሎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ስትራቴጂያዊ ፋይዳዎች አሉት።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የወንዞች የውሀ መጠን እየቀነሰ እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥ እየተባባሰ ባለበት የ21ኛው ክፍለ ዘመን የውሃ ሀብት ከነዳጅ ሀብት የበለጠ የዓለም አቀፍ ግንኙነት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እንደሚኖረው ይጠበቃል። ከዚህ አንጸር ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ ያላትን መብት እና ተጠቃሚነት ማሳደግ የሚኖረው ጂኦ-ፖለቲካዊ ጥቅም ከፍተኛ ነው።

በድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ዉሀ አጠቃቀም ታሪክ የላይኛው ተፋሰስ ሀገራት የበላይነት እና የተሻለ ተጠቃሚነት አላቸው። የአባይ ጉዳይ የተገላቢጦሽ ነው። 86 ከመቶ ውሀ የምታበረክተው ኢትዮጵያ ከአባይ ወንዝ ምንም ሳትጠቀም በወንዙ የመጨረሻ ጫፍ የምትገኘው ሀገር ሙሉ ለሙሉ በመጠቀም ልማቷን ስታፋጥን የዜጎቿን ህይወት ስትቀይር ዘመናት አልፈዋል። ይህ ኢ-ፍትሀዊ እና ኢ-ምክንያታዊ ታሪክ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊቀየር ይገባዋል። ሃገራችን ከአባይ ወንዟ የድርሻዋን የምታገኝበት ወቀት ላይ ደርሰናል። ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ላይ የጀመረችው የህዳሴ ግድብ ህጋዊ፣ ታሪካዊ፣ ምክንያታዊ እና ፍትሀዊም ነው። ሀገራችን የዓባይ ወንዝንም ሆነ ሌሎች ድንበር ተሻጋሪ ወንዞቿን የማልማት እና የመጠቀም ህጋዊ እና ተፈጥሯዊ መብቷን ለድርድር መቅረብ የለበትም።

ወደ መጠናቀቂያው እየተቃረበ ያለውን የህዳሴ ግድብ በአጭር ጊዜ ውስጥ አገባዶ ከግድቡ ተጠቃሚ ለመሆን ከፍተኛ ተሳትፎ እና ርብርብ ይጠይቃል። መንግስት የጀመረውን የዲፕሎማሲ (hydro-diplomacy) ስራ አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፣ በአንድ በኩል የግድቡን ህጋዊ እና ታሪካዊ ጥያቄ ለዓለም ማህበረሰብ በግልጽ ለማሳየት በሌላ በኩል በተለይ የግብጽን አፍራሽ እንቅስቃሴ እና ፕሮፓጋንዳ ለማክሸፍ ሰፊ ስራ ሊሰራ ይገባል። መንግስት ከአባይ ተፋሰስ ሀገራት በተለይም ከሱዳን ጋር ያለውን ግንኙነት ይበልጥ ማጠናከር፣ ቀጠናዊ እና አህጉራዊ ድርጅቶች ስለ ፕሮጀክቱ ያላቸውን ግንዛቤ የማሳደግ እና የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ስራዎችን አጠናክሮ መቀጠል አለበት። በግድቡ ውሀ አሞላል እና አጠቃቀም ወቅት የኢትዮጵያን ጥቅም በሚያስጠብቅ እና የተፋሰሱን ሀገራት ህዝቦች የውኃ ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊፈጸም ይገባል።

መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት በተለይም የብዙሀን መገናኛ ተቋማት፣ ባለሀብቶች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና መላው የሀገራችን ህዝቦች ግድቡ ተጠናቆ ዓባይን በነጻነት እና በእኩልነት የመጠቀም መብታችን እውን እንዲሆን የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል።

■■■

ከመሰናበቻው

የኮቪድ 19 ወረርሽኝና ፌደራሊዝም

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በዓለም ላይ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ህይወት የቀጠፈ ሲሆን ወረርሽኙ ካስከተለው የጤና ችግር በተጨማሪ የተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶችን ፈጥሯል። ወረርሽኙን ለመከላከል ፌደራላዊ እና አሀዳዊ የመንግስት አደረጃጀቶች ያላቸውን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ለመረዳት በመስኩ ባለሙያዎች ሰፊ ጥናት እየተካሄደ ሲሆን ጠንካራ የፌደራል ስርአት የዘረጉ ሀገራት ወረርሽኙን ለመከላከል የተሻለ አቅም እንዳላቸው ያለፉት ጥቂት ወራት ተግባራዊ ተሞክሮ ያመለክታል።

በፌደራል አገሮች ዘንድ የጤና ፖሊሲና ስትራቴጂ ማውጣትና መተግበር፣ የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣ የጤና አገልግሎት መስጠትና ለጤና አጠባባቅ ስራዎች በጀት ማዘጋጀት ወዘተ ለአንድ የመንግስት እርከን ብቻ የሚተው ጉዳይ አይደለም። የፌደራልና የክልል መንግስታት የየራሳቸው ስልጣንና ኃላፊነት ያላቸው ሲሆን፣ ብዙውን ጊዜ የፌደራል መንግስታት የጤና ፖሊሲ በማውጣት በኩል ጎላ ያለ ኃላፊነት ሲኖራቸው ክልሎች ደግሞ ፖሊሲውን በመፈጸምና ለህብረተሰቡ የጤና አገልግሎቶችን የመስጠት ኃላፊነት ይወስዳሉ።

በአሁኑ ሰአት የሀገራችን እና የመላው ዓለም ከፍተኛ የጤና ችግር የሆነውን ኮቪድ 19 ለመከላከል በሚደረገው እንቅስቃሴ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የፌደራል ስርአት የሚከተሉ ሀገሮች በማዕከላዊ መንግስት እና በክልል መስተዳድሮች መካከል ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር ውጤታማ ለማድረግ አደረጃጀታቸውን መፈተሽ ያስፈልጋል። በዚህ አጭር ጽሁፍ የኮቪድ 19 ወረርሽኝና ፌደራሊዝም ያላቸውን ግንኙነትና የፌደራል ስርአት የሚከተሉ ሀገሮችን ተሞክሮ እንዳስሳለን።



የዓለም ጤና ድርጅት በ2005 የመተንፈሻ አካል በሽታ የሆነውን ሳርስ (SARS) መከሰት ተከትሎ የዓለም አገራት ወደ ፊት ሊያጋጥም የሚችልን ወረርሽኝ ታሳቢ በማድረግ የጤና ስርዓታቸውን በቂ ምላሽ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ እንዲፈትሹ ጥሪ አድርጓል። ከዚህም አልፎ የዓለም ጤና ድርጅት ዓለም አቀፉን የጤና አጠባበቅ መመሪያ (International Health Regulation) እንደ ኮቪድ ያሉ የህብረተሰብ ጤና ችግሮች ሲያጋጥሙ የተማከለ ምላሽ አሰጣጥ ስርዓትን በሚያጎለብት መልኩ አሻሽሏል። ድርጅቱ በተለይ የፌደራል አገራት በወረርሽኝ ወቅት ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ጠንካራ እና ቀልጣፋ አሰራር እንዲገነቡ አስገንዝቧል።

እንደ ኮቪድ 19 ዓይነት ወረርሽኝ በባህሪው በሁለም እርከን ላይ የሚገኙ መንግስታትን ቅንጅታዊ አሰራር የሚፈልግ ሲሆን በአንዱ የመንግስት እርከን የሚወሰደው እርምጃ በሌላው እርከን ላይ ሊፈጥር የሚችለው ተጽእኖ ታሳቢ ሊያደረግ ይገባል። ያልተቀናጀ የውሳኔ አሰጣጥ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ወረርሽኙን ለመከላከል የሚወሰዱ እርምጃዎች የተወሰኑ ክልሎችን ይበልጥ ተጎጅ ሊያደርጉ ይችላሉ። ለምሳሌ እንቅስቃሴን የሚገድብ እርምጃ ኢኮኖሚው በቱሪዝም ላይ የተመሰረተውን ክልል የበለጠ ተጎጅ ሊያደርገው ይችላል። የፌደሬሽኑ አባል የሆኑት ክልሎች ለኮቪድ 19 ወረርሽኝ የሚኖራቸው ተጋላጭነት እኩል አይሆንም፣ አንዳንድ አካባቢዎች ከሌላው የበለጠ ተጋላጭ ሊሆኑ ይችላሉ። በተመሳሳይ ክልሎች ወረርሽኙን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እኩል አቅምም የላቸውም።

የፌደራል አገሮች ተሞክሮ

ያልተቀናጀ የፌደራል አሰራር አስከፊ ጉዳት አንዳንድ የፌደራል አገራት የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ለመቆጣጠር ባለፉት ጥቂት ወራት ባደረጉት እንቅስቃሴ ውስጥ በግልጽ ታይቷል። አሜሪካ፣ ስፔንና ብራዚል ለዚህ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። በአንጻሩ ጠንካራና የዳበረ የፌደራል ስርአት የገነቡ

ሀገራት ኮቪድ 19ን በመከላከል ረገድ የተሳካ ስራ መስራት የቻሉ ሲሆን ጀርመንና አውስትራሊያ ማሳያ ናቸው። በኮቪድ ወረርሽኝ ክፋኛ ከተመቱት ሀገራት ውስጥ አንዷ አሜሪካ ስትሆን ከመቶ ሺህ በላይ ዜጎቿን አጥታለች። ለዚህም ዋናው ምክንያት የችግሩን ግዝፈት በመረዳት ፈጣን እርምጃ በወቅቱ አለመወሰዱ መሆኑን በርካቶች ይስማማሉ። በአሜሪካ ፕሬዝዳንቱ የውጭ ዜጎች ወደ አገር እንዳይገቡ መከልከልና ድንበሮችን መዝጋት የሚያስችል ስልጣን ያለው ቢሆንም ዜጎች ከቤት እንዳይወጡ የማዘዝም ሆነ በየግዛቱ ያለውን እንቅስቃሴ መገደብ አይችልም። ይህን ማድረግ በዋናነት የክልሎች ስልጣን ነው። ሁሉም ግዛቶች በተመሳሳይ ጊዜ እርምጃ አለመውሰዳቸውና በፌደራል መንግስቱና በክልሎች መካከል ወጥነት ያለው እንቅስቃሴ አለመደረጉ ችግሩን አባብሶታል።

አንዳንድ ግዛቶች ለምሳሌ ካሊፎርኒያ፣ ኒው ጀርሲ፣ ኒወዮርክ የፌደራል መንግስቱን እርምጃ ሳይጠብቁ በራሳቸው የዜጎችን እንቅስቃሴ ለመገደብ መወሰናቸው፣ በኋላም የፌደራል መንግስቱ እንቅስቃሴ እንዲጀምሩ ያስተላለፈውን ትዕዛዝ ባለመቀበል እገዳውን ማራዘማቸው አሜሪካን ከከፋ ችግር ታድጓታል። የአሜሪካን ፌደራል ስርዓት በማጥናት የሚታወቁት ጆን ኪናሲድ አሜሪካ በኮቪድ 19 ክፋኛ እንድትጠቃ ያደረጋት በፕሬዝዳት ትራምፕ የሚመራው የማዕከላዊ መንግስት እና በክልሎች መካከል የተፈጠረው ፖለቲካዊ እሰጣገባ መሆኑን ይገልጻሉ።

በኮቪድ 19 ክፋኛ የተጠቃችው ሌላዋ አገር ስፔን ስትሆን ማድሪድ እና ካታሎኒያ ክፋኛ የተጠቁ አካባቢዎች ናቸው። ስፔን ያልተማከለ የጤና አገልግሎት ስርዓት የምትከተል ስትሆን የጤና አገልግሎቶችን መስጠት በዋናነት የክልሎች ኃላፊነት ነው። እስፔን በ2019 በወጣው የዓለም የጤና ኢንዴክስ በዓለም ላይ የተሻለ የጤና ስርአት ካላቸው አገራት አንዷ ነበረች። ከኮቪድ 19 በፊት በዓለም ሶስተኛ የነበረው የስፔን የጤና ስርዓት እስፔናውያንን ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ መታደግ አልቻለም። ኮቪድ 19 በስፔን መጀመሪያ ሲከሰት የክልሎች ድጋፍ የነበረው የፌደራል መንግስቱ የተማከለ የውሳኔ ሰጭነት ሚና ብዙም ሳይቆይ ችግር ውስጥ የገባ ሲሆን፣ በሂደት ለውሳኔ የሚረዱትን አስፈላጊ መረጃዎች ከክልሎች ማግኘት አልቻለም። በኋላም በፌደራልና በክልሎች መካከል እንዲሁም በክልሎች መካከል ቅንጅታዊ አሰራር መዘርጋት ባለመቻሉ ውጤታማ የነበረው የስፔን የጤና ስርዓት ለኮቪድ 19 ወረርሽኝ ተንበረከከ።



ብራዚሎችም የገጠማቸው ችግር ተመሳሳይ ሲሆን በፌደራል፣ በክልልና ከተማ አስተዳደር መንግስታት መካከል ጠንካራ በይነመንግስታት ግንኙነት (Intergovernmental Relations) አለመዘርጋቱ የኮቪድ 19 ትግላቸውን አሽመድምዶታል፡

> ከኮቪድ 19 በፊት በዓለም ሶስተኛ የነበረው የስፔን የጤና ስርዓት እስፔናውያንን ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ መታደግ አልቻለም።

ውጤታማ ተሞክሮ

አንዳንድ የፌደራል አገራት በፌደራልና በክልል መንግስታት መካከል ያለውን ግንኙነት የበለጠ በማጠናከር የኮቪድ 19 ወረርሽኝን በሚገባ መከላከል የቻሉ ሲሆን አውስትራሊያ እና ጀርመንን እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል። አውስትራሊያ ኮቪድ 19 ለመከላከል የዘረጋችው ጠንካራ የፌደራል ስርአት በእጅጉ ረድቷታል።The Council of Australian Governments በመባል የሚታወቀውና የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትርና የሁሉም ክልሎች አስተዳዳሪዎች አባል የሆኑበት ቋሚ የበይነመንግስታት ጉባኤ ወረርሽኙን ለመከላከል በማዕከላዊና በክልል መንግስታ መካከል የተቀናጀና ውጤታማ ስራ ለመስራት አስችሏል።

ጀርመን ከአውሮፓ ሀገራት ኮሮናን በመከላከል ውጤታማ ስራ በመስራት የተመሰከረላት ሌላኛዋ ሀገር ናት። ጀርመን ከኮቪድ 19 ጋር ያደረገችው እንቅስቃሴ ውጤታማ ይሆን ዘንድ በማዕከላዊና በክልሎች መካከል የተቀናጀ የበይነመንግስታት ግንኙነትና ትብብር ማዕቀፍ ተግባራዊ አድርጋለች። በመራሂተ መንግስት አንጌላ ሜርክል የሚመራው ማዕከላዊ መንግስት ከክልሎች ጋር በፈጠረው የተቀናጀ አሰራር በበሽታው የሚጠቁ እና የሚጃችን ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ለመቀነስ ተችሏል።

ከሌሎች ፌደሬሽኖች ምን እንማራለን?

የፌደራል ስርአት የምትከተለው ሀገራችን ወረርሽኙን በአስተማማኝ እና በተቀላፈጠ ሁኔታ ለመከላከል ከሌሎች የፌደራል ሀገራት ተሞክሮ በመውሰድ የኮቪድ 19 አደጋ ለመከላከል የሚያስችል ጠንካራ ስርአት መገንባት ያስፈልጋል።

በኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ ጉዳይ የፌደራልና የክልል መንግስታት የጋራ ስልጣን ሲሆን የፌደራል መንግስቱ የፖሊሲ ማዕቀፍና ስታንደርዶችን ያወጣል። የክልል መንግስታት የፌደራል መንግስት ያወጣውን ፖሊሲ የመፈጸምና ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይም የራሳቸውን ፖሊሲና ስታንዳርድ የማውጣት ስልጣን ያላቸው መሆኑን የህገመንግስቱ ድንጋጌዎች ያስረዳሉ። በዚሁ መሰረት የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ለመከላከልና ለመቆጣጠር በአገር አቀፍ ደረጃ የሚኒስትሮች ኮሚቴ ተቋቁሞል፣ ክልሎችም በተዋረድ የራሳቸውን የኮቪድ 19 መከላከል ግብረሃይል አቋቁመው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ።

የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ እንደሚያሳየው ኮቪድ 19 ወረርሽኝን ለመከላከል በማዕከላዊ እና በክልል መንግስታት መካከል የተቀናጀ አሰራር ያስፈልጋል። በሀገራችን የመጀመሪያው የኮቪድ ተጠቂ መጋቢት 6 2012 መገኘቱን ተከትሎ በፌደራልና በክልል መንግስታት እንዲሁም በከተማ አስተዳደሮች ጭምር የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን የሚገድቡ እርምጃዎች ተወስደዋል። እነዚህ በተለያዩ አካላት የተወሰዱ እርምጃዎች አንዳንዶቹ ያልተናበቡና ያልተማከሉ ከመሆናቸውም በላይ የህጋዊነት ጥያቄ ጭምር ያስነሱ ነበር። ከአንድ በላይ ክልሎችን የሚያገናኙ መሰረተ ልማቶችን መቆጣጠር የፌደራል መንግስቱ ስልጣን ቢሆንም ክልሎች በዚህ ጉዳይ ክልከላዎችን ሲያደርጉ ተስተውሏል።

> ከአንድ በላይ ክልሎችን የሚያገናኙ መሰረተ ልማቶችን መቆጣጠር የፌደራል መንግስቱ ስልጣን ቢሆንም ክልሎች በዚህ ጉዳይ ክልከላዎችን ሲያደርጉ ተስተውሏል።

እነዚህ ወጥነት በሌለውና ባልተማከለ ሁኔታ ሲወሰዱ የነበሩ እርምጃዎች የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከታወጀ በኋላ ወጥና የተቀናጁ እንዲሆኑ መደረጉ ወረርሽኙን ለመከላከል እንደ አንድ ጥሩ እርምጃ ሊወሰድ ይችላል። በመንግስት እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎችን ውጤታማነት ሙሉ ለሙሉ ለመገምገም ጊዜው ገና ቢሆንም የሌሎች አገራት ልምድ እንደሚያሳየው በፌደራልና በክልል መንግስታት እንዲሁም በክልሎች መካከል ጠንካራና የተቀናጀ ግንኙነትና የትብብር ማዕቀፍ እንዲሁም የህዝብን ጥቅም የሚያስቀድም ጠንካራ የፖለቲካ አመራር ኮቪድን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እጅግ አስፈላጊ ነው።

በፌደራል ደረጃ ባለው ብሄራዊ የኮቪድ 19 ምላሽ አሰጣጥ ግብረ ኃይል ክልሎች፣ በክልል ደረጃ ባለው ግብረ ኃይል ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች የሚሳተፉበትን አሰራር መፍጠር ይገባል። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባለ ጠንካራ የበይነመንግስታት ግንኙነት በሌለበት እና የክልሎች አቅም ውስን በሆነበት ፌደራሽን ውስጥ በብሄራዊ ኮቪድ 19 አስተባባሪ ግብረ ኃይል ውስጥ የሚኖረው የክልሎች ተሳትፎ የተቀናጀ አሰራር ለመዘርጋት ከማስቻሉም በላይ በክልሎች መካከል የጎንዮሽ ትብብር ለመፍጠር ሁነኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

ክልሎች ለወረርሽኙ የሚኖራቸው ተጋላጭነትና ወረርሽኙን ለመቆጣጠር ያላቸው አቅም የሚለያይ በመሆኑ የፌደራል መንግስት ለክልሎች የሚያደርገው ድጋፍ የተጋላጭነት መጠናቸውንና ወረርሽኙን ለመከላከል ያላቸውን አቅም ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባል። በተመሳሳይ ክልሎችም በስራቸው ላሉ ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች የተጋላጭነት መጠንን መሰረት ያደረገ ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል። እንዲሁም በአጎራባች ክልሎች መካከል የጋራ ግብረ ኃይል በማቋቋም መረጃ መለዋወጥ ብሎም ሀብትን በጋራ ለመጠቀም ጥረት ማድረግ ይገባል። በአጠቃላይ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን መከላከልና መቆጣጠር የሚቻለው ጠንካራ ትብብራዊ ፌደራሊዝም (Cooperative federalism) ስርአትን በማጠናከር እና የህዝብን ጥቅም በሚያስቀድም ጠንካራ የፖለቲካ አመራር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። የሀገራችን ፖለቲካ የጀርባ አጥንት የሆነው የፌደራል ስርአት ኮቪድ 19 ጨምሮ ሌሎች ማህበራዊ ችግሮቻችንን ለመፍታት በሚችል መልኩ ይበልጥ ሊጠናከር እና ሊደራጅ ይገባል።

■■■



ዐሳብ ሜዳ

ሰብአዊ መብትና የዴሞክራሲ ስርአት

የሰብአዊ መብት ትርጓሜ

“መብት” እና “ሰብአዊ መብት” የሚሉት አገላለፆች እየተቀያየሩ ሥራ ላይ ሲውሉ ይስተዋላል። “መብት” የሚለው ቃል በአጠቃላይ ለተፈጥሮ “ሰው” እና በህግ የሰውነት ደረጃ የተሰጣቸው “ተቋማት” ያላቸውን መብት የሚያመለክት ሲሆን “ሰብአዊ መብት” ለተፈጥሮ ሰው ማለትም ለሰብአዊ ፍጡር የተሰጡ መብቶችን ያመለክታል። ሰብአዊ መብት አንድ ሰው ሰው በመሆኑ ብቻ የሚቀዳጀው፣ ከልደቱ እስከ ህልፈቱ የሚጎናጸፈው፣ በጊዜ እና ቦታ የማይገደብ መብትን ያካትታል። በህይወት የመኖር፣ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ የመስራት እና ሀብት የማፍራት፣ ከፍርሀት ነጻ የመሆን፣ ቤተሰብ የመመስረት፣ በህግ ፊት እኩል የመሆን፣ ጥገኝነት የማግኘት፣ ወዘተ ከሰብአዊ መብቶች ጥቂቶቹ ናቸው።

ዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብት ህጎች እና ስምምነቶች መንግስታት ሰብአዊ መብትን የማክበር፣ የመጠበቅና የማሟላት ግዴታዎች እንዳሉባቸው ይደነግጋሉ። የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች እና አንቂዎችም እነዚህን ድንጋጌዎች ለማስከበር ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ። ሰብአዊ መብቶችን ማስጠበቅ ትኩረት እንዲያገኝ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ዜጎችን ከመንግስታት ህገ ወጥ የመብት ረገጣ ለመጠበቅ ነው። ሰብአዊ መብቶችን ለመጠበቅና ለመከላከል ሀገራት ከሚያወጧቸው ህጎች እና ደንቦች በተጨማሪ በዓለምአቀፍ ደረጃ ልዩ ልዩ ደንቦች የጸደቁ ሲሆን እ.ኤ.አ በ1948 የወጣው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ አንዱ ነው።

የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች መሰረታቸው የተፈጥሮ ህጎች ሲሆኑ ፍልስፍና ባህል እና ሃይማኖታዊ አስተምህሮቶች በሰብአዊ መብት ህጎች አረዳድ ላይ ከፍተኛ ግብአት ሆነው አገልግለዋል። “ተፈጥሯዊ መብቶች” የሚባሉት ሰው ሰራሽ ያልሆኑ፣ በተፈጥሮ የተቀዳጇቸው መብቶች ሲሆኑ ሁሉም ሰብአዊ ፍጡራን ሊኖራቸው የሚገቡ፣ በማንም ሊገፈፉ የማይችሉ መብቶች ናቸው። የተፈጥሮ ህግን መሰረት ያደረጉ ንድፈ ሃሳብ አቀንቃኞች የሰብአዊ መብቶች መነሻ መሰረቶች ተፈጥሯዊ የሞራል፣ የሃይማኖት፣ ወግና ልማዶች ናቸው ብለው ያስባሉ።

ሰብአዊ መብት ታሪካዊ ዳራ

የሰብአዊ መብት መርሆዎች የረዥም ጊዜ ታሪክ ያላቸው ሲሆን ከ6ኛው ክፍለ ዘመን (ከክርስቶስ ልደት በፊት) ጀምሮ የሚታወቁ እንደሆነ በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎች ይናገራሉ። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት መርሆዎች ታሪካዊ መነሻ አድርጎ የሚያስቀምጠው ጊዜ በ539 (ከልደት በፊት) ሲሆን በዚያ ወቅት የፐርሺያ ኢምፓየር ንጉስ የነበረው ታላቁ ሳይረስ (Cyrus the Great) ባቢሎንን በጦርነት አሸንፎ ካስገበረ በኋላ ባወጣው አዋጅ ባሪያዎችን ነፃ አድርጎ ያሰናበተበትን ታሪካዊ አጋጣሚ ያወሳል። በግዛቱ የሚኖሩ ዜጎች ሁሉ የፈለጉትን ሃይማኖት የመምረጥ መብት እንዳላቸውም ደንግጎ የዘር ልዩነት እንደማይደረግ ማወጁም ይነገራል። እነዚህ በቅርጻ ቅርጽ ላይ ተጽፈው የተገኙ የሰብአዊ መብት መሰረታዊ ሃሳቦች እ.ኤ.አ በ1948 በወጣው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ድንጋጌ የመጀመሪያዎቹ አራት አንቀፆች ሆነው እንዲሰፍሩ ተደርገዋል።

ከዚህ በተጨማሪ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት በኩል የሰብአዊ መብት መርሆዎችን የያዙ ሰነዶች ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው። በ1215 በእንግሊዙ ንጉስ ኤድዋርድ የተዘጋጀው ማግናካርታ፣ በ1222 በሀንጋሪ አስተዳደር የተዘጋጀው “the Golden Bill of Hungary”፣ በ1320 በስኮትላንድ የተዘጋጀው “Declaration of Arbroath”፣ በ1789 የወጣው የፈረንሳይ “Declaration of the Rights of Man and of the Citizen”፣ 1789–1791 የተዘጋጀው የአሜሪካ “Bill of Rights” እና በመጨረሻም በ1948 የወጣው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌ (Universal

Declaration of Human Rights) ይገኙበታል - ሁሉም ዓመታት እ.ኤ.አ ናቸው።

የሰብአዊ መብት ዘርፎች

የሰብአዊ መብት ሰፊ አድማስ እና ትርጓሜ ያለው ጽንሰ ሀሳብ ሲሆን ልዩ ልዩ የዘርፉ ባለሙያዎች በተለያየ መንገድ በመከፋፈል ይገልጹታል። ሰብአዊ መብቶችን በእድሜ፣ በጾታና በሙያ ከፋፍሎ ማየት አንዱ ሲሆን የህፃናት መብት፣ የሴቶች መብት፣ የሰራተኞች መብትን... ያጠቃልላል። የግለሰብ እና የቡድን መብት፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብት፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል መብቶች ሌሎች የመብት አይነቶች ናቸው። በሰብአዊ መብት ላይ ጥናት የሚያካሂዱ ባለሙያዎቹ እነዚህን የመብት አይነቶች በሶስት መድበው አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ትውልድ ሰብአዊ መብቶች በማለት ይከፋፍሏቸዋል። ቀጥሎ በዝርዝር እንመለከታቸዋለን።

የመጀመሪያው ትውልድ (First Generation) የሰብአዊ መብት የሚባሉት መሰረታዊ የሆኑ እና ሰው በመሆን ብቻ የሚገኙ ከላይ የዘረዘርናቸውን የመብት አይነቶች የሚያካትት ሲሆን፣ ነጻነትንና የፖለቲካ ተሳትፎን የሚያጠቃልሉ በህግ ፊት እኩል የመሆን መብት፣

> ከዚህ አንጻር የግለሰብ ወይስ የቡድን መብት ይቅደም የሚሉ ውይይቶች የሰብአዊ መብቶችን በተሟላ መልኩ ካለማወቅ እና እርስ በርሳቸው ያላቸውን ጠንካራ መስተጋብር በቅጡ ካለመረዳት የሚነሱ ናቸው።

ፍትህ የማግኘት መብት፣ የሃይማኖት ነፃነትና አምልኮ እንዲሁም የመምረጥ መብት የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። የመጀመሪያ ትውልድ መብቶቹ "ሰማያዊ መብቶች" (Blue Rights) ተብለው ይታወቃሉ።

የሁለተኛው ትውልድ (Second Generation) የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች በዋናነት ከእኩልነት ጋር የተያያዙ መብቶች ሲሆኑ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶችን የሚመለከቱ ናቸው። ከነዚህ በተጨማሪ ምቹ የስራ ቦታ፣ መጠለያ ምግብና ጤና የመሳሰሉትም መብቶች በዚሁ ትውልድ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። ሁለተኛው ትውልድ መብቶቹ "ቀይ መብቶች" (Red Rights) የሚል ስያሜ አላቸው።

ሦስተኛው ትውልድ (Third Generation) የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች ከግለሰብ ይልቅ በጋራ ጥቅም ላይ የሚውሉ መብቶችን የሚያካትት ሲሆን የቡድን መብት፣ የአነሳዎች (Minrities) መብት፣ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት፣ የተፈጥሮ ሀብትን የማልማት እና የመጠቀም መብት እና የመሳሰሉትን የሚመለከት ሲሆን "አረንጓዴ መብቶች" የሚል ስያሜ አላቸው።

ከላይ የተዘረዘሩት የመብት አይነቶች እርስ በራሳቸው የተያያዙ እና የማይነጣጠሉ ናቸው። አንዱ የመብት አይነት ከተጣሠ ሌሎቹ የመብት አይነቶች ሙሉ ለሙሉ ሊከበሩ አይቸሉም። ለምሳሌ የግለሰብ እና የቡድን መብት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሲሆኑ፣ አንደኛው መብት ከተጓደለ ሌላው ሊሟላ ፈጽሞ አይችልም። ከዚህ አንጻር የግለሰብ ወይስ የቡድን መብት ይቅደም የሚሉ ውይይቶች የሰብአዊ መብቶችን በተሟላ መልኩ ካለማወቅ እና እርስ በርሳቸው ያላቸውን ጠንካራ መስተጋብር በቅጡ ካለመረዳት የሚነሱ ናቸው።

የሰብአዊ መብት አያያዝ በኢትዮጵያ

የሀገራችን የሰብአዊ መብት አያያዝ ታሪክ በዓለምአቀፍ ደረጃ እጅግ ዝቅተኛ ከሚባሉት ሀገሮች ተርታ የሚመደብ ነው። የኢትዮጵያ መንግስታት በዜጎች ላይ እጅግ ዘግናኝ ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶችን ፈጽመዋል - ከህግ ውጪ ግድያ፣ እስርና ግርፋት፣ ያለክስ ለተራዘመ ጊዜ ማቆየት በዜጎች ላይ ያለገደብ የሚፈጽሟቸው ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶች ናቸው። ዜጎች በፖለቲካ አመለካከታቸው፣ በብሄራቸው፣ በኃይማኖታቻው ወይም በሌላ ማንነታቸው ምክንያት ሰብአዊ መብቶቻቸው ተጥሶ ለከፋ እና አሰቃቂ ግፍ ይዳረጋሉ። በዜጎች ላይ በተፈጸሙ ኢ-ሰብአዊ እርምጃዎች አያሌ ወገኖቻችን ህይወታቸውን አጥተዋል፣ አካላቸው ጎድሏል፣ ሀብት ንብረታቸውን አጥተዋል።

የሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አለመከበር ሀገራችንን ብዙ ዋጋ አስከፍሏታል - ሰብአዊ እና ፖለቲካዊ ቀውስ፣ አመጽ፣ የእርስ በርስ ጦርነት፣ የኢኮኖሚ ድቀት፣ ከብዙ በጥቂቱ ይገኙበታል። የሀገራችን የሰብአዊ መብት አያያዝ ያለበትን አስከፊ ደረጃ በተመለከተ የተለያዩ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች የሚያወጧቸው ሪፖርቶች አመላካች ሲሆኑ፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በኢትዮጵያ ያለውን የሰብአዊ መብት አያያዝ አስመልክቶ በቅርቡ ይፋ ያደረገው ሪፖርት ለዚህ ሁነኛ ማሳያ ነው። ከዚህ አንጻር በሀገራችን የሰብአዊ መብት አያያዝን ለማሻሻል ሰፊ እና የተቀናጀ ስራ መስራት ያስፈልጋል።

ሰብአዊ መብትና ዴሞክራሲ

የሰብአዊ መብት መከበር ቀጣይነት ላለው የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እጅግ አስፈላጊ ነው። የተሳካ የዴሞክራሲ ስርአት ለመገንባት የሰብአዊና መሰረታዊ መብቶችን መጠበቅና መደገፍ ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ ያልቻለ የፖለቲካ ስርአት ትርጉም ባለው መልኩ ዴሞክራሲን አስፍኗል ለማለት አይቻልም። በዴሞክራሲያዊ ሰርዓት እያንዳንዱ ዜጋ የመምረጥ፣ የመመረጥ፣ የመደራጀት እንዲሁም መሪዎቹን የመሰየም እና የመሻር መብት አለው። በአንድ ሀገር ውስጥ የሰብአዊ መብቶች መከበር በዚያ ሀገር ያለው የዴሞክራሲ ስርአት አንዱ እና ዋነኛው መገለጫ ነው። ዝቅተኛ የሰብአዊ መብት አያያዝ ታሪክ ያላቸው ሀገሮች ዝቅተኛ የዴሞክራሲ መለኪያ (ኢንዴክስ) ያላቸው ሲሆን ይህም በሁለቱ ጽንሰ ሀሳቦች መካከል ያለውን ጠንካራ ቁርኝት ያሳየል። በሀገራችን ጠንካራ የዴሞክራሲና የፖለቲካ ስርአት ለመገንባት በሚደረገው እንቅስቃሴ የሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ማክበር ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

■■■

ሃፃ ወግ

የህገ መንግስት ትርጓሜ

ሂደት እና ውጤት

ከኮቪድ 19 ምክንያት ምርጫ 2012 መራዘሙን ተከትሎ በሀገራችን ከተፈጠረው የህግ እና የፖለቲካ አጣብቂኝ ለመውጣት ነኢፓን ጨምሮ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት አማራጭ ሀሳቦች ማቅረባቸው ይታወሳል። ከመፍትሄዎቹ መካከል የህገ መንግስት ማሻሻያ ማድረግ፣ የህግ መንግስት ትርጓሜ መጠየቅ፣ የሽግግር መንግስት ማቋቋም፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጅ እና ፓርላማውን መበተን የሚሉ ይገኙባቸዋል። አማራጭ ሀሳቦች በፓርቲዎች ቢቀርቡም በቂ ውይይት ሳይካሄድባቸው በገዢው ፓርቲ የቀረበው "የህገ መንግስት ትርጓሜ መጠየቅ" የሚለው አማራጭ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅ ተደርጓል። የህገ መንግስት ትርጓሜው ከሌሎች በርካታ አማራጮች የተሻለ ስለመሆኑ፣ የትርጉም አሰጣጥ ሂደቱ ግልጽነት እና አሳታፊነት እንዲሁም በውጤቱ ዙሪያ በርካቶች ጥያቄ እና ስጋታቸውን የገለጹ ሲሆን ውሳኔውን ብዙዎች ግልጽነት እና አሳታፊነት የጎደለው ሲሉ ተቃውመውታል።

ከምርጫ መራዘም ጋር ተያይዞ በተፈጠረው አጣብቂኝ ዙሪያ ለመወያየት ጠቅላይ ሚንስትሩ ከጥቂት የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ለመወያየት ያዘጋጁት መድረክ ገና ከጅምሩ የመንግስትን አግላይነት በግልጽ ያሳየ ነበር። በጣት የሚቆጠሩ ፓርቲዎችን በአጭር ቀጠሮ እና አጀንዳው ለተሰብሳቢዎች ቀድሞ ባልተገለጸ ሁኔታ ሰብስቦ "ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ውይይት ተካሄደ" ማለት ግልጽነት እና ኃላፊነት የጎደለው አሰራር ነው። ምርጫን በሚያክል ቁልፍ ሀገራዊ እና የዴሞክራሲ አጀንዳ



ለሚዲያ ግብአት በሚሆን መልኩ ስብሰባ ጠርቶ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ውይይት ተካሄደ ማለት ከለውጡ ቀደም ሲል የነበረውን የፖለቲካ ባህል ከመድገም ያለፈ ፋይዳ የለውም።

በተዘጋጀው መድረክ ላይ "በገለልተኛ" ባለሙያዎች ተዘጋጀ ተብሎ በቀረበው ጽሁፍ፣ ከአጣብቂኙ ለመውጣት አራት አማራጮች እንዳሉ እና "የህገ መንግስት ትርጓሜ መጠየቅ" የተሻለ አማራጭ እንደሆነ ተገልጾ ፓርቲዎች እንዲስማማሙ ተጠየቀ። አብዛኛዎቹ የተፎካካሪ ፓርቲዎች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለማሳለፍ ፓርቲዎች የየራሳቸውን የመፍትሄ ሀሳብ ይዘው እንዲቀርቡ ጊዜ እንዲሰጥ ቢጠየቅም፣ እጅግ በተፋጠነ ሁኔታ የመንግስት የውሳኔ ሀሳብ ለፓርላማ ከዚያም አልፎ ለህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ እንዲቀርብ ተደረገ። ወትሮም በመንግስት ላይ ያላቸው እምነት እያቆለቆለ የመጣው የተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ ከምርጫ መራዘም ጋር ተያይዞ የተፈጠረውን ቅርቃር ለማለፍ መንግስት የሄደበት መንገድ ኢ - ዴሞክራሲያዊ ሲሉ ብዙዎች ኮንነውታል።

የህገ መንግስት ትርጓሜ ሂደት

የህገ መንግስት ትርጓሜውን ተግባራዊ ለማድረግ የትርጉም ጥያቄው በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በኩል ለህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የቀረበ ሲሆን ጉባኤው ስራውን ሲያካሂድ ቆይቶ በሰኔ ወር መጀመሪያ የውሳኔ ሀሳቡን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት አቅርቦ ምክር ቤቱ አጽድቆታል፥ የህገ መንግስት አጣሪ ጉባኤው በአዋጅ ቁጥር 798/2005 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትርጉም የተጠየቀባቸውን የህገ መንግስቱን ሶስት አንቀጾች ለመተርጎም የተለያዩ ባለሙያዎችን ሀሳብ እና አስተያየት ለመቀበል የምክክር ጉባኤ ያዘጋጀ ሲሆን፣ በውይይቱ ላይ የህገ መንግስት ባለሙያዎች እና ህገ መንግስቱ ሲረቀቅ የተሳተፉ ግለሰቦች ተገኝተዋል።

ሙያዊ አስተያየት የመሰብሰቡ ሂደት

የህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 798/2005 አንቀጽ 9 ጉባኤው በቀረበለት የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ ወይም ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሀሳብ ከማቅረቡ በፊት አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ተቋማት ወይም ባለሙያዎች ቀርበው አስተያየት እንዲሰጡ ሊያደርግ እንደሚችል በግልጽ ያስቀምጣል።

ይሁን እንጂ የህገ መንግስት ባለሙያዎችን የውሳኔ ሀሳብ ለመስማት የተዘጋጁት መድረኮች ግልጽ እና አሳታፊ እንዳልነበሩ የሚገልጹ በርካታ አስተያየቶች እና ተቃውሞ ቀርበዋል። የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርቡ የተጋበዙ ባለሙያዎች ፖለቲካዊ ገለልተኝነት እና ብቃትን አስመልክቶ

ብዙዎች ስጋታቸውን ገልጸዋል። በአተረጓጎም ሂደቱ ላይ በርካታ ጥያቄዎች ተነስተዋል። የተጠቀሱትን አንቀጾች ለጉባኤው የተላኩት አንቀጾች ትርጉም ያስፈልጋቸዋል? ባለድርሻ አካላት በበቂ ሁኔታ ተሳትፈዋል? የሚሉ እና ሌሎችም ጥቄዎች ይገኙባቸዋል። በእነዚህ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ በርካታ ምሁራን የተለያዩ አቋሞች የነበሯቸው ሲሆን የመሰማት እድል ያገኙት የመንግስን አቋም የደገፉት ብቻ ናቸው የሚለው አስተያየት ከሚዲያዎች እና ሌሎች አካላት ቀርቧል።

አጣሪ ጉባኤው የህገ መንግስት ምሁራን የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርቡ የሰጠው የጊዜ ገደብ እጅግ አጭር በመሆኑ አማራጭ ሀሳቦች በበቂ ሁኔታ እዲቀርቡ እድል የሚሰጥ አልነበረም። በመድረኩ ላይ ተገኝተው አስተያየታቸውን ለመስጠት የጠየቁ ምሁራን በርካታ እንደነበሩ የተገለጸ ሲሆን እድል አግኝተው የተሳተፉ ጥቂቶች እና የመንግስትን አቋም የሚያጠናክሩ ብቻ ነበሩ ማለት ይቻላል። በባለሙያ የቀረቡት አስተያየቶች በአብዛኛው ተመሳሳይ እና የገዢውን ፓርቲ አቋም ለማጠናከር ተመርጠው የቀረቡ ናቸው የሚል አስተያየት እንዲፈጠር አድርጓል።

በተዘጋጁት የአስተያየት መቀበያ መድረኮቹ አማራጭ እና ተቃራኒ

> **ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ማለት በሚቻ ሁኔታ፣ ከጥቂቶች በስተቀር፣ በአንድ ድምጽ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ስጋት ባለበት ሁኔታ ምርጫ ማካሄድ እንደማይቻል ተስማምተዋል።**

ሀሳቦችን እንዲስተናገዱ እድል አለመሰጠቱ የአጣሪ ጉባኤውን ገለልተኝነት በብዙዎች ዘንድ አጠያያቂ እንዲሆን አድርጎታል። ከምርጫ ጋር በተያያዘ የህገራችንን መጻኢ የፖለቲካ አቅጣጫ ለመወሰን የተሻለ አማራጭ ለተባለው "የህገ መንግስት ትርጉም" የመስጠት ስራ በቂ ጊዜ እና አማራጭ ሀሳቦች እንዲቀርቡ አለመደረጉ ገና ከጅምሩ ሂደቱ ቅቡልነት እንዳይኖረው አድርጓል።

በምርጫ መራዘም ምክንያት የተፈጠረው ችግር የህግ እና የፖለቲካ ገጽታ እንዳለው እየታወቀ ህገ መንግስቱን በህገ መንግስት ባለሙያዎች ብቻ በማስተርጎም ለችግሩ መፍተሄ ለማበጀት የተሄደበት አግባብ ከጅምሩ የተሳሳተ እንደሆነ አብዛኞቹ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ገልጸዋል። ህገ መንግስት የፖለቲካ እና የህግ ሰነድ ነው። በስራ ላይ ያለው የህገራችን ህገ መንግስት የደርግ መንግስት በወደቀ ማግስት ሲረቅ እና ሲጸድቅ በዋናነት የተሳተፉት በጊዜው የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ናቸው - ህገ መንግስቱ የፓርቲዎቹ ድርድር እና ስምምነት ውጤት ነው። በመሆኑም ህገ መንግስቱን በመተርጎምም ሆኑ በማሻሻል ሂደት ቀጥተኛ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል።

በምርጫ መራዘም ምክንያት የተፈጠረውን ፖለቲካዊ እና ህጋዊ ቀውስ ለመፍታት በሚደረግ ውይይት ዋነኛ ባለድርሻ የሆኑት የተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በትርጉም ሂደቱ ላይ እንዲሳተፉ ተደጋጋሚ ጥያቄዎች ቢቀርቡም መንግስት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ በሂደቱ እንዳይሳተፉ ተደርጓል። "የህገ መንግስት ትርጉም መጠየቅ" የሚለው አማራጭ ሲመረጥ ሀሳባቸው ያልተሰማው የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በትርጉም አሰጣጥ ሂደቱ ላይም ድርሻ እንዳይኖራቸው መደረጉ ገዢው ፓርቲ እና መንግስት ለተፎካካሪ ፓርቲዎች ያላቸውን ግምት በግልጽ የሚያሳይ ነው።

የህገ መንግስት ትርጓሜ ውጤት

ግልጽነት እና አሳታፊነት በጎደለው መልኩ የተካሄደው የትርጉም አሰጣጥ ሂደት ተጠናቆ ውጤቱ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅ ተደርጓል። በውጤቱም ቀጣዩ ጠቅላላ ምርጫ ኮቪድ 19 የጤና ስጋት አለመሆኑ ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ ከዘጠኝ ወር እስከ አንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንዲካሄድ የተወሰነ ሲሆን ምርጫ ተካሂዶ የስልጣን ሽግግር እስኪፈጸም ድረስ በስራ ላይ ያሉት የፌዴራል እና የክልል ምክር ቤቶች እንዲሁም አስፈጻሚ አካላት በስራ ላይ እንዲቆዩ ተወስኗል።

ውሳኔው ቀጣዩ ምርጫ ዓለም አቀፍ የጤና ድርጅቶች የኮሮና ቫይረስ ስርጭት በተመለከተ የሚያደርጉትን ጥናት እና የሚሰጡትን ውሳኔ መሰረት በማድረግ የጤና ሚኒስቴር፣ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እና የሳይንሱ ማህበረሰብ ኮቪድ 19 የጤና ስጋት አለመሆኑን ካረጋገጡበት እና ይህም በምክር ቤቱ ከጸደቀ ከዘጠኝ ወር እስከ አንድ አመት ባለው ጊዜ ውስጥ እንደሚሆን ይደነግጋል።

ምክር ቤቱ ያሳለፈው ውሳኔ በመርህ ደረጃ ቀደም ሲል የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሲያቀርቡት ከነበረው የውሳኔ ሀሳብ ጋር ተቀራራቢ ነው። ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ማለት በሚቻ ሁኔታ፣ ከጥቂቶች በስተቀር፣ በአንድ ድምጽ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ስጋት ባለበት ሁኔታ ምርጫ ማካሄድ እንደማይቻል ተስማምተዋል። ኮቪድ 19 ከመከሰቱ በፊትም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አባል የፖለቲካ ድርጅቶች እና ጥምረቶቹ ምርጫው እስከ አንድ አመት ድረስ እንዲራዘም ሃሳብ ማቅረባቸው ይታወቃል።

የኮሮና ወረረርሽኝ እና የህዳሴ ግድብን ጨምሮ ሌሎች ቁልፍ ሀገራዊ አጀንዳዎችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመጠበቅ ጠንካራ ማዕከላዊና የክልል መንግስታት እንደሚያስፈልጉ የሚያምኑ የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች የፌደራል እና የክልል ህግ አውጪ እና አስፈጻሚ አካላት የስራ ዘመናቸው እስከ አንድ አመት እንዲራዘም ስምምነታቸውን በገለጹበት ሁኔታ መንግስት አጀንዳውን በብቸኝነት እና አግላይ በሆነ መልኩ ለመወሰን የሄደበት አግባብ ሀገራዊ መግባባት ለመፍጠር በሚደረገው እንቅስቃሴ ያለው ፍላጎት አናሳ መሆኑን በግልጽ አረጋግጧል።

ኮሮናን በአስተማማኝ ሁኔታ ተከላክለን የሀገራችንን ውስብስብ እና በርካታ የልማት እና የፖለቲካ ጥያቄዎች በአጭር ጊዜ ለመመለስ በተለይም በመንግስት በኩል ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር በትብብር ሊሰራ ግድ ይላል። በለውጡ ማግስት ገዢው ፓርቲ ቀድሞ "ተቃዋሚ ፓርቲ" ብሎ የሚጠራቸውን "ተፎካካሪ ፓርቲ" የሚል ስያሜ በመስጠት የፈነጠቀውን አዲስ የፖለቲካ ምእራፍ ለማጠናከር መንግስት ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር በትብብር የመሰራት ታሪካዊ ተጠያቂነት አለበት፣ ፣ ከምርጫ መራዘም ጋር ተያይዞ ገና ያልተመለሱ ጥያቄዎችን እና ሌሎች በሂደት የሚነሱ የህዝብ እና የፖለቲካ ኃይሎች የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ መንግስት አሁን እየሄደበት ካለው አግላይ እና "እኔ አሻግራችኋለሁ" ዘይቤ ተላቆ ብሄራዊ መግባባትን ለመፍጠር የሚያስችል አቅጣጫ ሊከተል ይገባል።

■ ■ ■

መጻጉ ገፅታ

ጌሪማንደሪንግ (Gerrymandering)

ጌሪማንደሪንግ ማለት ስልጣን ላይ ያሉ ፖለቲከኞች ቀጣዩን ምርጫ ለማሸነፍ በሚያስችላቸው መንገድ የምርጫ ክልሎችን እንደአዲስ የሚያደራጁበት መንገድ ነው። የቃሉ ስያሜ እ.ኤ.አ. በ1812 የማሳቹሴትስ ገዥ ከነበረው Elbridge Gerry ጋር ይያያዛል። ጌሪ በወቅቱ ገዥ በነበረበት ግዛት ውስጥ የሪፐብሊካን ፓርቲን በሚጠቅም መልኩ የምርጫ ክልሎች እንዲደራጁ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል።

በዚህ መልክ ከተደራጁት የምርጫ ክልሎች ውስጥ አንዱ ባልተለመደ መልኩ ረጅም ከመሆኑም በላይ ቅርጹ እንሽላሊት (salamander) ይመስል ነበር። በዚህ የተበሳጩት ፌደራሊስቶች የስቴት ገዥውን ስምና የምርጫ ክልሉን ቅርጽ የምትመስለውን ተሳቢ እንስሳ (Gerry and Salamander) ስያሜ በማጣመር ድርጊቱን ጌሪማንደሪንግ በማለት ሰይመውታል። ከዛ ጊዜ ጀምሮ እስከአሁን ድረስ በአሜሪካ ፖለቲካ ውስጥ ቃሉ ሆነ ተግባሩ አጀንዳ ሁኗል።

ጌሪማንደሪንግ ነጻና ፍትሃዊ የሆነ ትክክለኛ ምርጫ እንዳይደረግ ለማድረግ ከሚሰሩ የፖለቲካ አሻጥሮች ውስጥ አንዱ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ተግባሩ በሁሉም የዓለማችን ክፍል የተለመደ ሁኗል። ጌሪማንደሪንግ በዋናነት የሚፈጸመው ስልጣን ላይ ባለው መንግስት ነው። ዓላማውም ስልጣን ላይ ያለው አካል ቀጣዩን ምርጫ ማሸነፍ እንዲችል ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው። በመሆኑም ለዚህ ዓላማ ሲባል የምረጫ ክልሎች እንደአዲስ ይደራጃሉ፤ ወሰናቸውም እንደ አዲስ ይሰመራል።

በዋናነት ጌሪማንደሪግ በሁለት መንገድ ሊፈጸም ይችላል። ተመሳሳይ ፍላጎትና አስተሳሰብ ያላቸው አካባቢዎች ተመሳሳይ ፓርቲን ይደግፋሉ ተብሎ ይገመታል። በዚህ ግምት መነሻነት በተለይ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ይደግፋል/ሊመርጥ ይችላል ተብሎ የሚታሰብን አካባቢ ወይም የምርጫ ክልል በመበታተን ወደ ሌሎች የምርጫ ክልሎች እንዲካለል በማድረግ የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊዎች ድምጽ እንዲዋጥ/እንዲባክን ሊደረግ ይችላል።

ይህ ዘዴ የአብላጫ ድምጽ (first-past -the post) የምርጫ ሥርዓትን በሚከተሉ አገሮች ስልጣን ላይ ያለው አካል በቀላሉ እንዲያሸንፍ ያደርገዋል። ስልጣን ላይ ያለው አካል በአዋሳኝ የምርጫ ክልሎች ያሉትን በቁጥር አነስተኛ የሆኑ የራሱን ደጋፊዎች በማሰባሰብና ወደ አንድ የምርጫ ክልል በማምጣት በቀላሉ የሚያሸንፍበትን አዲስ የምርጫ ክልል ሊፈጥር ይችላል። እነዚህ ደጋፊዎች ቀድመው በነበሩበት የምርጫ ክልል በቁጥር አናሳ በመሆናቸው የሚሰጡት ድምጽ ስልጣን ላይ ያለውን አካል ለዳግም ድል አያበቁትም ነበር።

ወይም በአዋሳኝ ምርጫ ክልሎች የሚገኙ ስልጣን ላይ ላለው አካል ተገዳዳሪ የሆኑ የተቃዋሚ ደጋፊ አካባቢዎችን ወደ አንድ ምርጫ ክልል በማጠቃለል ሌሎች ምርጫ ክልሎችን ለራስ ድል አስተማማኝ እንዲሆኑ ሊደረግ ይችላል። ምንም እንኳን ተቃዋሚ ፓርቲዎች በዚህ አዲስ በተደራጀው የምርጫ ክልል እጅግ አብላጫ በሆነ ድምጽ ቢያሸንፉም በውክልና ወንበራቸው ላይ የሚያመጣው ለውጥ ስለማይኖር ስልጣን ላይ ላለው አካል የሚፈጥረው ስጋት አይኖርም።

በአጠቃላይ ጌሪማንደሪንግ የምርጫ ክልል አከላለልን ለራስ ድል በሚመች መልኩ በማዋቀር የምርጫ ውጤትን ቀድሞ ለመቆጣጠር (manipulate) ስራ ላይ ከሚውሉ መንገዶች አንዱ ነው። የጌሪማንደሪግ ሀሳብ አዲስ የምርጫ ክልል አከላለል በፖርቲዎች የፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይ ቀጥተኛ የሆነ እንደምታ ስላለው በብዙ ሀገሮች በከፍተኛ ጥንቃቄ እና ስምምነት የሚሰራ ቁልፍ የፖለቲካ እና የምርጫ ስራ ነው።

ጌሪማንደሪንግ በኢትዮጵያ

ጌሪማንደሪንግ በሀገራችን መቼ እና እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ ብሎም በምርጫ ውጤት ላይ ያስከተላቸውን ለውጦች በሌላ ጊዜ የምናየው ይሆናል። እስከዚያው ገዢው ፓርቲ ህዝቦች የሚያነሷቸውን የአስተዳደር ክልል ጥያቄ ከጌሪማንደሪንግ አስተሳሰብ በራቀ እና የህዝቦችን ህገ መንግስታዊ መብት በሚያከብር መንገድ ማየት እንዳለበት ማስታወስ ያስፈልጋል።

ምንም እንኳን ደቡብ ክልልን እንደ አዲስ የማዋቀር ጥያቄዎች በቀጥታ የምርጫ ክልሎችን ከማደራጀት ጋር የሚያያዝ ባይሆንም የጌሪማንደሪንግ አይነት ዓላማና ውጤት እንደማይኖረው ማረጋገጥ ይገባል።

በመሆኑም ጉዳዩ የህዝቦችን ፈቃድ መሰረት ባደረገና ራስን በራስ የማስተዳደር መብትን በሚያረጋግጥ መልኩ መታየት ይኖርበታል። ደቡብ ክልልን እንደ አዲስ የማደራጀት ጉዳይ የህዝቦችን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት እውን እንዲሆን ከማድረግ ባለፈ ምርጫን ታሳቢ ያደረገ ፖለቲካዊ ግብ (ጌሪማንደሪንግ) እንደሌለው ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

■■■